

# ትምህርት ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

## ቅዱስ መስቀል

መስቀል በመጽሐፍ ቅዱስ በሦስት ይከፈላል።

1) መከራ መስቀለ ክርስቶስ
2) መከራ መስቀለ ክርስቲያን
3) ዕፀ መስቀል

### መከራ መስቀል ክርስቶስ

መከራ መስቀል ክርስቶስ ማለት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ከጐልጎታ እስከ ቀራንዮ አደባባይ፣ ከዚያም እስከ ርደተ መቃብር የደረሰበት ጽኑ መከራ መስቀል ይባላል። የመስቀል ትርጉም ቅሉ መከራ ማለት ነው።

> የእግዚአብሔር ቃልም የመስቀሉ ነገር (የክርስቶስ በመስቀል መከራ የመቀበሉ ነገር) ለሚጠፉ ሞኝነት ነው ለእኛ ለምናምን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው። (፩ኛ ቆሮ ፩፥፲፰)

ጌታችን በበረት መወለዱ፣ በጨርቅ መጠቅለሉ፣ በብርድ መንከራተቱ መስቀል ነው። ወደ ግብጽ ተሰዶ እኛን ከስደተ ነፍስ መመለሱ፣ ሰይጣንን ከሰዎች ልቦና ማሳደዱ መስቀል ነው። ጻድቀ ባሕሪይ ሲሆን ኃጥእ መባሉ፣ የአእምሮ ጌታ ሲሆን እብድ፣ ሳምራዊ መባሉ ሁሉ መስቀል ነው። እኛ ከብረንበታል እርሱም ተፈትኖበታል። ጨርቅ መታጠቁ ግንድ መሸከሙ፣ የአይሁዳውያንን ስድብ መታገሱ፣ ዓይኑን ሸፍነው እየመቱ ማን መታህ ተናገር ነብይ ከሆንክ እያሉ ሲዘብቱበት መታገሱ መስቀል ነው።

በአጠቃላይ ስለ እኛ የተቀበለው መከራ ሁሉ መከራ መስቀል ይባላል። የእግዚአብሔር ቃልም የመስቀሉ ነገር (የክርስቶስ በመስቀል መከራ የመቀበሉ ነገር) ለሚጠፉ ሞኝነት ነው ለእኛ ለምናምን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው። (፩ኛ ቆሮ ፩፥፲፰)።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በገላቲያ መልእክቱ በአብርሃም ልጅነታችን በግርዘታችን እንድናለን፣ የክርስቶስ ሞት ምንም አያደርግልን በሚሉት ቢጸ ሃሳዊያን ላይ «እኔ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መከራ መስቀል እንጂ በሌላ አልመካም» ብሏል (ገላ ፮፥፲፬)። ሐዋርያው በኤፌሶን መልእክቱም «በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ በመስቀሉ ሰላምን አደረገ» ብሏል። (ኤፌ ፪፥፲፮)። ከዚህ በላይ የተመለከትናቸው ጥቅሶች በክርስቶስ መከራ መስቀል የሚተረጎሙ ናቸው። ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም በዘወትር ጸሎትዋ መስቀል ኃይላችን ነው፣ መስቀል ጽንዐ ነፍሳችን ነው፣ መስቀል ቤዛችን ነው፣ መስቀል የነፍሳችን መድኃኒት ነው፣ አይሁድ መከራው ለእኛ አይደለም ብለው ካዱ፣ እኛ ግን አመንን፣ ያምንን እኛም በመስቀሉ ኃይል ዳንን ትላለች። ይህ የክርስቶስ መከራ ዘወትር በልብ የሚታሰብ እንጂ በዓይነ ሥጋ የማይታይ ስለመሆኑ «አኮ ከመ ይትርአይ ዝንቱ መስቀል አላ ከመ ይትኃላይ - ይህ መስቀል [መከራ ክርስቶስ] በዓይን የሚታይ ሳይሆን በልብ የሚታሰብ ነው ይላል። (መጽሐፈ ኪዳን)።

ስለዚህ ሕማሙንና ሞቱን እያሰብን እንደ ዮሐንስ ልንጸና ይገባናል። ቅዱስ ያሬድም መድኃኒት ስለሆነችው ስለሞቱና ስለመስቀሉ ሲናገር «ዝንቱ ውእቱ መስቀል በአማን ዕፀ ያቀልል ... ኃይልነ ወጸወንነ ወሞገስነ» ይላል። በዚያው ክፍል «በኃይለ መስቀሉ ገብረ መድኃኒተ ሰደደ አጋንንተ አንሥአ ሙታን በኃይለ መስቀሉ ፈትሐ ሙቁሐነ - መስቀሉ ኃይል መድኃኒትን አደረገ አጋንንትን አሳደደ ሙታንን አስነሳ እስረኞችን ፈታ» ይላል። እንዲሁም «በመስቀሉ አርኀወ ወገነተ - በመስቀሉ ገነትን ከፈተ» አለ። በተጨማሪም «በመስቀሉ ወበቃሉ ገብረ ለነ ሰላመ ክርስቶስ መድኃኒነ ... እንዘ ዝርወነ አስተጋብአነ

በመስቀሉ ኮነ ሕይወትነ - መድኃኒታችን ክርስቶስ በመስቀሉና በቃሉ ሰላምን አደረገልን የተበተንነውን በመስቀሉ ሰበሰበን ሕይወትም ሆነን» ብሏል። በተመሳሳይ መንፈስ «ዝንቱ መስቀል ረድኤት ለእለ ነአምን ሕይወት ለአይሁድ ስደት - ይህ መስቀል ለምናምን ረድኤትን ሕይወት ለአይሁድ ስደት ነው» በማለት ይዘምራል።

## መከራ መስቀለ ክርስቲያን

መከራ መስቀለ ክርስቲያን ማለት አንድ ክርስቲያን ወይም ሐዋርያ ስለ ክርስቶስ ስም ስለ ወንጌል ስለ ቤተ ክርስቲያን እድገት ስለ ማኅበረ ምእመናን የሚደርስበት መከራ ስድብ ሃሜት መስቀል ይባላል። መድኃኒታችን ሲናገር «መስቀሉን የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ የእኔ ሊሆን አይገባውም» አለ (ማቴ ፲፥፴፰)። በሌላ ክፍል «እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር እራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ» አለ (ማቴ ፲፮፥፳፬ ። ማር ፰፥፴፬-፴፮)። ጌታችን ሲናገር መስቀሌን ሳይሆን መስቀሉን ተሸክሞ ይከተለኝ እንዳለ ልብ እናድርግ። ቅዱሳን ሰዎች የሚቀበሉት መከራ የክርስቶስ ሳይሆን የእነርሱ ነው። በመሆኑም ቅዱስ ጴጥሮስ ቁልቁል መሰቀል፣ የቅዱስ ጳውሎስ በሰይፍ መመታት፣ የቅዱስ ጊዮርጊስ በመጋዝ መተርተር፣ የቅዱሳን ሁሉ ልዩ ልዩ ጸዋተወ መከራ መስቀል ይባላል።



እንባቢ ሆይ፥ አንተስ ስለ ስሙ መከራ ደርሶብህ ያውቃልን? ስለ ስሙ ተሰደሃል? ወይስ በሥጋ ሥራ ነው የምትታማው? … ለመሆኑ በዘመናችን ስለ ወንጌል የታሰሩ ስሙ ሕይወት መድኃኒት ነው ብለው በመስበካቸው መከራ የሚቀበሉ ያሉ ይመስልሃል? ወይስ ወህኒዎች ሁሉ በዓለም ወንጀለኞች ብቻ ተሞልተዋል? በል አንተ መከራ ከገጠመህ ታገስ።

## ዕፀ መስቀል

ዕፀ መስቀል ከእንጨት የተሰራ መስቀል ማለት ነው። የውርደት ምልክት የነበረው መስቀል የድል አርማ ሆኗል። እንዴት ቢሉ፥

- መድኃኒታችን በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ ሰላምን ስላደረገ (ቆላ ፩፥፳)
- መድኃኒታችን እኛን ለማዳን የውርደት ሞት ያውም በመስቀል ላይ ሞቶ ሞትን ድል የነሳበት የድል አደባባይ ስለሆነ (ፊሊ. ፪፥፰) ነው።
- ስለ ዕፀ መስቀል በተጨማሪ (ማቴ ፳፯፥፵፪ ። ዮሐ ፲፱፥፳፩) ይመልከቱ።

እንባቢ ሆይ፥ ታዲያ ዕፀ መስቀሉን ለምን እንደምናከብረው እንደምንሳለመው ታውቃለህ? አንዳንድ ሰዎች አባትህ ተወግቶ የሞተበትን ጩቤ ብታገኘው የአባትህ ደም የፈሰሰበትን ጩቤ ትስመዋለህን? እያሉ ሲያጣጥሉ አልገጠመህም? (ፊል ፫፥፲፯-፳፩) መስቀሉን የምናከብረው ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህናት ሆኖ ያገለገለበት መቅደስ በግ ሆኖ ስለ እኛ ራሱን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሰዋበት ምስዋዕ (መንበር)፣ የጽድቅ ማዕከል ሰማያዊው ሊቀ ካህናት የክህነት አገልግሎት ያጠቃለለበት ደብተራ መስቀል ስለሆነ ደሙ ስለፈሰሰበት፣ መርገመማችን ስለ ተሻረበት እንደሆነ አስተውል።

ቅዱስ አትናቴዎስ «በምድር ላይ ኃጢአትን አሳፈረ፣ በሲኦል ሞትን አሸነፈ፣ በመስቀል ላይ መርገምን ሻረ፣ በመቃብር ውስጥ ፈርሶ በስብሶ መቅረትን አስቀረ» ብሎ እንደተናገረ።

አባትህ የሞተበትን እንዴት ትስመዋለህ ማለታቸው ከንቱ አሉባልታ ነው። ለመሆኑ በመስቀል ማነው የሞተ? በመስቀል ጌታ አልተሸነፈበትም። አባታችን በመስቀል ጠላት ዲያቢሎስን ገደለ፣ መርገምን ሻረ፣ ሞትን ሞት ድል ነሳ እንጂ።

ስለዚህ መስቀል ክርስቶስ ዲያቢሎስን ድል የነሳበት መሳሪያ ጠላታችን የሞተበት መሳሪያ ነው እንጂ አባታችን የተሸነፈበት አይደለም። በመሆኑም የድላችን ምልክት ነው። በእንጨት (በመስቀሉ) እንዴት ኃይል ያደርጋል ቢሉህ ደግሞ የሙሴ በትር ቀይ ባሕርን ከከፈለ (ዘዳ ፲፬፥፳፩)፤ የኤልያስ መጠምጠሚያ ዮርዳኖስን ከከፈለ (፪ኛ ነገ ፪፥፲፱)፤ የቅዱስ ጳውሎስ ጨርቅ ጋኔን ካወጣ (የሐዋ ሥራ ፲፱፥፲፩-፳)፤ የጌታችን ቀሚስ ደም ካቆመ ደሙ የፈሰሰበት መስቀል እውር ቢያበራ፣ ሙት ቢያስነሳ፣ የሚያስደንቀው የት ላይ ነው በላቸው። በሁሉ የሚሠራ አምላክ አንድ ነውና።

እግዚአብሔር በመስቀል ኃይሉ ይጠብቀን።

*በመምህር ልዑለ ቃል አካሉ*